የካቲት ፲ 2002 ዓ/ም
ቁጥር: D/B-STO/0003/10
ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክርስቲያን
ሕጋዊዉ ቅዱስ ሲኖዶስ ጽ/ቤት

ጉዳዩ፡- የብጹዕ አባታችን ሊቀ ዻዻስ አቡነ ዜና ማርቆስን ዜና እረፍት ስለሰማን ኃዘናችንን መግለጽ

እኛ በሚኒሶታ የደብረ ብርሃን ቅዱስ ዑራኤል ቤ/ክርስቲያን ካህናትና ምእመናን የታላቁን መንፈሳዊ አባት ሊቀ ጳጳስ አቡነ ዜና ማርቆስ እረፍት በመስማታችን ጥልቅ ኃዘን የተሰማን መሆኑን እንገልጻለን። የብፁዕ ሊቀ ጳጳስ አቡነ ዜናማርቆስ የሕይወት ታሪክ በኃይለ መንፈስ ቅዱስ የተገነባ፣ግዙፍና አንጸባራቂ ስለሆነ በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ በጉልህ የሚታወቅ እንደመሆኑ ምጠን በዚህ አጋጣሚ ዘርዝሮም ሆነ ጨልፎ ለማቅረብ ቦታዉም ሆነ ጊዜዉ እንደማይፈቅድልን እናምናለን።

ሆኖም ብፁዕ አቡነ ዜናማርቆስ ከልጅነት እስከ እለተ እረፍት ክቡር ሕይወታቸዉን ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን እድገትና ልማት ለማበርከት ቆርጠዉ በመነሳት የገዳም ኑሮን እየኖሩ ደዋትዎ ድካምን ድል በማድረግ ፣እንዲሁም ትምህርተ ወንጌልን በማስተማርና በመስበክ ፣በሊቀ ጵጵስናቸዉ የሲኖዶስ ሰብሳቢ በመሆን አርቆ ማስብን የተላብሰ ሁለገብ ርትአዊ አስተዳደርን በማስፈን የተመሰከረላቸዉ ፣ በመጨረሻም በቤተ ክርስቲያኒቱ ዉስጥ በተፈጠረዉ ኢቀኖናዊ የሆነ ሰይጣናዊ የሥልጣን አወራረስ ሁከት በመፈጠሩ በስደት ሲኖሩ ታላቅ ቤተክርስቲያን አቋቁ.
ስለዚህ ሐዋርያዊዉ ቅዱስ ጳዉሎስ በመልእክቱ, «መልካም ተጋድሎን ተጋደልኩ፣እንግዲህስ እግዚአብሔር የሚሰጠኝን የጽድቅ አክሊል እጠብቃለሁ» እንዳለዉ ይህን የጽድቅ አክሊል ለቸርነቱ ወሰን የሌለዉ አምላክ ለታላቁ ሐዋርያና ሰማዕት ለሆኑት የቅድስት ቤተክርስቲያን ታላቅ አባት ለብፁዕ ሊቀ ጳጳስ አቡነ ዜናማርቆስ እንዲያድልልን በጸሎተ ፍትሐት እየዘየቅን ቅድስት ነፍሳቸዉን ከቅድሳን ጋር እንዲያኖርልን እንለምናለን።

ወስብሀት ለእግዚአብሔር!!

ግርማ ይስማው
የሰበካ ጉባኤ ሊቀመነበር።